# Seattle Fire Department

የአደጋ ጊዜ ምላሽ የአየር ቴክኖሎጂ

## ቴክኖሎጂው ምንድነው?

Seattle Fire Department፣ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የአደጋ ጊዜ ምላሽ የአየር ቴክኖሎጂ (Emergency Response Aerial Technology, ERAT) ወይም ድሮኖችን ወደ እሳት አደጋ ማጥፋት፣ የማዳን እና የአደጋ ጊዜ የሕክምና ምላሽ መሳሪያዎች ማከል ሀሳብ ያቀርባል። የሚጠበቀው የERAT ክልል መላውን ከተማ የሚሸፍን አገልግሎት ይሰጣል።

የSeattle Fire Department (SFD) ERAT በአንድ የSFD የእሳት አደጋ ጣቢያ ጣሪያ ላይ ይቀመጣሉ፤ እንዲሁም በFire Alarm Center አማካኝነት ወደ ስራ ይሰማራሉ/ይንቀሳቀሳሉ።

ሲላክ፣ ERAT ካሜራው ወደ አድማስ አቅጣጫ እንዲያነጣጠር ተደርጎ በተቀመጠለት ኬክሮስ (latitude) እና ኬንጋሮስ (longitude) ይበራል። ልክ በቦታው እንደደረሰ፣ ካሜራው ወደ ወደታች እንዲያመለክት ይደረጋል፤ ይህም ስልጠና የወሰዱ የSeattle የእሳት አደጋ የአደጋ ቁጥጥር አመራር እና አሰማሪዎች የቀጥታ ስርጭት እንዲያገኙ፣ የአሠራር ውሳኔዎችን እንዲመለከቱ እና እንዲወስኑ ይረዳል። ከቀጥታ ስርጭት የሚመጣው ቪድዮ በምንም ሁኔታ አይቀረፅም ወይም አይቀመጥም። የድሮኑን ቀጥታ ስርጭት ከ SFD ምላሽ ሰጪዎች በስተቀር ሌላ ማንም አያየውም። ድሮኑ የሚቀረፀው ቪድዮ፣ SFD ለማንኛውም የህግ ማስፈፀምያ ተግባር አይጠቀምበትም። ከማንኛውም የክትትል መሣሪያዎች ጋር አይገናኝም (surveillance tools)።

## ቴክኖሎጂው የምንጠቀመው ለምንድነው?

ERAT፣ የእሳት አደጋ መከላከያ ተቋማት የሰዎችን ህይወት ለማዳን እና ንብረትን ለመጠበቅ የሚጠቀሙበት ጠቃሚ እና አዲስ መሳሪያ ነው። የSFD፣ ERAT ለማህበረሰቡ የአደጋ ጊዜ ምላሾቻችን እና ውጤቶቻችን እንዴት ማሻሻል እንደሚችል ሲገመግም ቆይቷል።

በተወሰኑ አከባቢዎች፣ ERAT ወደ አደጋው ቦታ ቀድሞ በመድረስ፣ እሳት ለማጥፋት ወይም ለነፍስ አድን ስልቶቻችን ወሳኝ የሆነ መረጃ ለSFD ሊያቀርብ ይችላል። እንዲሁም፣ የእሳት አደጋ ሰራተኞችን/የአስቸኳይ ጊዜ ህክምና ባለሙያዎች (Emergency Medical Technicians, EMTs) እና በአደጋው ቦታ ላይ ወይም አጠገቡ ያሉ ሰዎችን የበለጠ ለመጠበቅ ይረዳል። ከባድ አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ፣ እንደ ድልድዮች፣ ሆስፒታሎች እና ትምህርት ቤቶች ያሉ ወሳኝ መሠረተ ልማቶችን መቃኘት ይችላል። የSFD አደጋ ምላሽ ሰጪዎች፣ ወደ አደጋው ቦታ ለመንዳት የሚጠቀሙባቸው መንገዶች ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ ይችላል።

SFD፣ የአየር ላይ እይታ የማሻሻል አቅሙን የሚያሻሽል እና ለምላሽ ሰጪዎች እና ለህዝቡ የበለጠ ደህንነትን የሚሰጥባቸውን በርካታ የአደጋ ዓይነቶች ለይቷል። ERAT ጥቅም ላይ ሊውልባቸው የሚችሉ ሁኔታዎች ምሳሌ፡- በህንፃዎች እና በከፍተኛ ቦታዎች ላይ የሚነሱ እሳቶች፣ የውሃ ማዳን፣ የቁጥቋጥ እሳት፣ አደገኛ ቁሳቁሶች እና የኃይል ምላሾች፣ እንዲሁም ከመሬት መንቀጥቀጥ በኋላ።

## ስብስብ

ከአየር ላይ የሚነሳው የቀጥታ ስርጭት ምስል አይያዝም ወይም አይቀመጥም። የቀጥታ ስርጭት ምስል፣ ከሌሎች መምሪያዎች ወይም ኤጀንሲዎች ለሚመጡ ሰዎች ወይም ለህዝብ አይጋራም ወይም አይታይም።

የERAT አቅራቢ ድርጅት ደህንነቱ በተጠበቀ ሰርቨር ላይ ይሰበሰባል እንዲሁም ይከማቻል ብለን የምገምተው መረጃ፡- እንደ የበረራዎች ብዛት፣ በስራ ላይ የነበረበት ሰዓት፣ የተጓዘው ርቀት እና የጥገና ሁኔታ ያሉ ስለ በረራው እና ስለ ድሮኑ የሚገልጹ መለኪያዎች። የኮንትራት ቋንቋ፣ የከተማውን የመረጃ ቴክኖሎጂ (Information Technology, IT) ቋንቋ ይከተላል፤ ይህም የመረጃ ምስጠራን እና ያልተፈቀደ መዳረሻን እና አጠቃቀምን ለመከላከል ጥበቃዎችን ይጠይቃል።

## መከላከያዎች

የSFD ERAT አስተባባሪዎች/ኦፕሬተሮች፣ ከፌዴራል አቪዬሽን አስተዳደር (Federal Aviation Administration, FAA) ምስክር ወረቀት ያላቸው እና ሁሉንም ስልጠናዎች እና መስፈርቶች የሚያሟሉ ይሆናሉ። የSFD የእሳት አደጋ ሰራተኞች የቀጥታ ስርጭቱ ከSFD የክስተት ቡድን ማዘዣ እና ከላኪዎች ውጭ በማንኛውም ሰው እንዳይታይ ለመከላከል የግላዊነት ስልጠና እንዲሁም የፖሊሲ እና የአሠራር ሂደቶችን ይከተላሉ። በውሉ መሰረት፣ ሻጩ ድርጅት ቴክኒካል ችግር ለመፍታት ካልሆነ በስተቀር የቀጥታ ስርጭቶች እንዳይመለከት እና ከ SFD ውጭ ላለ ማንኛውም ሰው እነዚህን መረጃዎች እንዳያጋራ ይከለከላል። የERAT የቀጥታ ስርጭት ምስሎች፣ ግለሰቦችን ለመለየት ጥቅም ላይ አይውሉም፤ ዓላማው የእሳት አደጋ መከላከያ፣ የቴክኒክ ማዳን እና ምላሽ ለመምራት፣ የመዋቅር ጉዳትን ለመገምገም ወይም ህይወት አድን መሳሪያዎችን ለማጓጓዝ ለSFD የአደጋ ቁጥጥር አመራር መረጃ በመስጠት ላይ የተወሰነ ነው።

## አስተያየት መስጫ ጊዜ

አስተያየት መስጫ ጊዜ፣ ከ ሐምሌ 13 - ነሐሴ 12፣ 2026 ነው። SFD በአስተያየት መስጫ ጊዜው ውስጥ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት፣ ሁለት በአካል የሚደረጉ እና ሁለት በበይነ መረብ የሚካሄዱ ስብሰባዎችን እያዘጋጀ ነው።

አስተያየትዎ በ Seattle.gov/Surveillance ማቅረብ ይችላሉ። ሁሉም አስተያየቶች፣ በዚህ ቴክኖሎጂ ላይ በተመሠረተው የክትትል ተጽዕኖ ሪፖርት (Surveillance Impact Report) ውስጥ ተካተው ወደ Seattle City Council ይቀርባሉ። አስተያየት ከሚሰጥበት ጊዜ ውጭ አስተያየት መስጠት ከፈለጉ፣ እባክዎን በ seattle.gov/council ላይ ያሉትን ኢሜይሎች በመጠቀም በቀጥታ ለከተማው ምክር ቤት ያስገቡ።